**ልጅህንም ወደ እኛ ሰደድከው ከአንተ ዘንድ ሳይለይ መጣ ከአንተ ሳይነቃነቅ ሄደ። በምድር ከወላጁ ጋር ሳለ በሰማይ ከአባቱ ጋር ተቀመጠ ከላይ ሳይጎድል ከታች ሳይጨመር ወረደ።**

**ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ቁጥር ፴-፴፮**

## የሚያቃጥል እሳት
## ሥጋን ተዋሐደ፣

ገብርኤል ተልኮ ብሥራት ሳይናገር፣
ዜናው ሳይሰማ የመምጣትህ ነገር፣
እረኞች ሳያዩህ በግርግም ተኝተህ፣
የሰው ልጅ ሳትባል ከድንግል ተወልደህ፣

አንደበት የሆንከው ኢሳይያስ ሲናገር፣
ሰማዮችን ቀደህ ውረድ ይልህ ነበር።
ከአንተ ሌላ ማንም ሰውን መች ረዳው፣
የገዛ ክንድህ ነው መድኃኒት ያመጣው።

ዳርቻ ፍጻሜ የሌለህ አምላክ ነህ፣
ማንም የማያውቅህ ማንም ሰው ያላየህ።
ያገኙህም የለም ደግሞም የሚያገኝህ።
መንግሥትህ አያልቅም አይሻርም ኃይልህ።
አያልቅ አይጨረስ ገናንነት ክብርህ፣
ከቶ አይሠወርም የአንተስ ጌትነትህ።
አንተን የሚያውቅ የለም ከራስህ በስተቀር
ለአንተ ግን ግልጽ ነው አባት ሁሉም ነገር።

ጥንት እና ዳርቻ በፍጹም የሌለህ፣
ለሁሉ ፍጻሜ አንተ ትሰጣለህ።
ሁሉ ስላንተ ነው በሁሉ ስፍራ አለህ፣
ከልዑላን ይልቅ እግዚአብሔር ልዑል ነህ።
በአንድ ልጅህ መምጣት ያፈረን ጎበኘህ፣
በይቅርታህ ብዛት የራቁትን ቀርበህ።
ከራቁት ሩቅ ነህ ስውር በመሆንህ፣
በአንተ ተሠውሯል ገናንነት ኃይልህ።
በውስጥም በውጪም በሁሉ ቦታ አለህ፣
ሁሉን ቻይ ነህና አንተን በአንተ ጋርደህ።

የወለድከው ልጅህ ስለ አንተ ነገረን፣
እርሱ ነው ዜናህን ለእኛ ያደረሰን።
እንዳንተ እንደ አባቱ አንተ እንደከበርከው
ልጅህም እንዲሁ ዘላለም ክቡር ነው።
ስለ ወልድ ነገር የአንተን አባትነት፣
የሰማን ከአንተ ነው ምስክርን በእውነት።
ለአንተም ለልጅህም ስግደት ይሰገዳል፣
እኩል ነው ክብራችሁ መበላለጥ የታል።
በአብ እና በወልድ በእናንተ መካከል፣
ዕለት ሰዓት የለም መቅደም መከታተል።
አባት በመሆኑ አብ ከልጁ አይበልጥም፣
ልጅም በመሆኑ ወልድ ከአብ አያንስም።

በሥውር በጎቡእ አንተን ለማግኘት ሰው፣
አይወጣም አይዋኝም ስለማይቻለው።

ለአንዳፍታ ለሰዓት ለዓይን ጥቅሻ ያህል፣
ማንም ሊመረምር ሊገነዘብ አይችል።
ለማወቅ ይከብዳል ነገር ሁኔታውን፣
በአብ እና በወልድ መካከል ያለውን።
ሕያውና ቅዱስ የሚሆን መንፈስህ፣
ጥልቅነቱን ያውቃል ስለ መለኮትህ።

የተዋሐዶን ነገር ከእርሱ ተምረን ነው
የአንድነት ሦስትነት ምሥጢርን ያወቅነው።
ለአንዳፍታ እንኳ አይጠፋም እኩልነታችሁ
ከቶ አይበተንም ይኽ አንድነታችሁ፣
ደርሶ እንደማይለይ የግብራችሁ ነገር፣
ማንም አልነገረን ከመንፈስህ በቀር።

ሁሉን ሳትደክም ትሸከመዋለህ፣
ለሁሉ ሳታጎድል ትመግበዋለህ፣
ደግሞም ዝም ሳትል ሁሉን ታስባለህ፣
በጎ ቅን አሳቢ ቸር አምላክ አንተ ነህ።
ለሁሉ ስትሰጥ ካንተ አንዳች አይጎድልም፣
ሁሉን ስታረካ አንተ ግን አትነጥፍም፣
ለሁሉ ያለህን ትተውለታለህ፣
አንተ ሳትቀበል የምትሰጥ ጌታ ነህ።
ክቡር ነህ ዘላለም ባዕድ የማይሰጥህ፣
አንተ ፈጣሪ ነህ ማንም የማያዝህ።



እግዚአብሔር ልጅህን ወደኛ ሰደድከው፣
ከአንተ ጋር እያለ ከአንተ ሳትለየው።
ሁለንተናው ሲኖር አንተ ካለህበት፣
ሳይለይህ መጣ እኛ ካለንበት።
በምድር ከእናቱ ጋር አብሯት እየኖረ፣
ከአባቱ ጋር ደግሞ በሰማይ ነበረ።
ከሰማይ ሳይጎድል ሳያንስ ከቁጥር፣
ከታች ሳይጨመር ወረደ ወደ ምድር።
መምህረ ወንጌል አምላኩ ለጴጥሮስ፣
ለዓለም መድኅን የሆንክ ኢየሱስ ክርስቶስ፣

ከሰማይ የወረድክ ረጅም ፈትል ነህ፣
ምድር በመምጣትህ ከአብ ያልተለየህ።
ይኽ ምሥጢር ታላቅ ነው ከሁሉ በለጠ፣
እግዚአብሔር በሥጋ አሜን ተገለጠ።
ሥጋዊ ፍጥረትን ሁሉን የፈጠረ፣
የፍጥረታት ጌታ በማኅፀን ኖረ።
የሚያቃጥል እሳት ሥጋን ተዋሐደ፣
ሥውር የማይታይ ገሐድ ተወለደ።



ብርሃን ተጎናጽፎ መኖር የሚቻለው፣
በግርግም ተኝቶ ጨርቅ ጠቀለለው።
እንደ አምላክነቱ ሁሉን እየሠራ፣
በምድር ክርስቶስ እንደ ሰው ተጠራ።

ታላቅ የምስራች በዳዊት ከተማ፣
ከእግዚአብሔር መላእክት ለእረኞች ተሰማ።
ክርስቶስ የሚባል መድኃኒት ተወልድዋል፣
ሄዳችሁ አግኙት በግርግም ተኝትዋል።

በማለት ተናግረው ምስራች አብስረው፣
ወደ ሰማይ ወጡ እረኞቹን ትተው።

የመላእክቱን ቃል ሰምተው የተረዱ፣
ቤተ ልሔም ድረስ ወልድን ሊያዩት ሄዱ።
እንደ መላእክቱ ቃል ግርግም የደረሱት፣
ዮሴፍን ድንግልን ጌታንም አገኙት።
የማይመረመር ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፣
ወልድን ለማግኘት ነው እዚህ የመጣነው።
ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታችን ባለበት፣
አብራ ትገኛለች ድንግል ማርያም በእውነት።

የታመነ ቃል ነው መቀበል ያለብን፣
ክርስቶስ ተወልድዋል ኃጢአተኞች ሊያድን።
ለእኔም ለአንተም ለአንቺም ለሕፃናቱም ነው፣
ወልድ ሥጋ ለብሶ ምድር የወረደው።

ኢሳይያስ ተናግሯል እንዳንጠፋ በዓለም፣
ያለ ዋጋ ብሉት ይኼን ሥጋ እና ደም።

መልክ ረጋፊ ነው ዕድሜም ታይቶ ጠፊ፣
ወንድሜ አትታለል እኅቴ አትስነፊ።
ተወለደ ብቻ ብንለው አይበቃም፣
ለመዳን ካልቀረብን ከእስር አንፈታም።

ያለ ዋጋ ሰጥቶን መመገብ ካቃተን፣
ሰዎች የፍርድ ቀን ማምለጫም ቃል የለን።
ድግስ ተደግሶ ሰው ቤት ከተጠራን፣
እንበላ የለም ወይ ማዕድ እያነሳን።
ያን የጠራንን ሰው ጥሪውን አክብረን፣
ከቀረበው ምግብ አብረን እንቆርሳለን።

በመድኃኔዓለም ቤት ሁልጊዜ ድግስ ነው፣
ሁሉም ሰው ተጋብዞ በዩው ግን ጥቂት ነው።
የአብርሃም ልጆች ነን ብለው የተመኩት፣
አይሁድ መልስ አጥተዋል ጌታን ያናገሩት።
አባታችን ብቻ ማለት በቂ አይደለም፣
እንደ አብርሃም ሁኑ ብሏል መድኃኔዓለም።
ደፍረን ብንናገር እኛም ተመክተን፣
ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶልናል ብለን፣
ለብቻው አይጠቅምም ስላወራን አንድን፣
ለሥጋው ለደሙ በእምነት ካልቀረብን።

ቃል ገብተን እንውጣ እውነት ነው እያልን፣
ከቁርባኑ ሳንወስድ የታል መዳናችን።
ክርስቶስ ሲወለድ ስጦታ ለመጡት፣
ወርቅ እጣን ከርቤውን ይዘው ለቀረቡት፣
ጌታ ተቀብሏል የእጅ መንሻቸውን፣
ስጦታውን ሳይንቅ ከሰው የመጣውን።

የኛንም ዝማሬ የኛንም ምስጋና፣
ዛሬም ይቀበላል የእጅ መንሻ ነውና።
እኛም እንቀበል ከቅዱሱ ቦታ፣
ሥጋ ወደሙ ነው የእግዚአብሔር ስጦታ።/፰/

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር!**
**አብርሃም ሰሎሞን**
**ታኅሣሥ ፳፱/፳፻፬ ዓ.ም።**